ምን ዓይነት አእምሮ ነው?
አካሉ ድረሴ

አቶ አይምሮ ዳኛቸው የተባሉ ሰው በኢትዮሚዲያ ድረ-ገፅ ላይ "የሚፈርስ ከተማ ነጋሪት ቢጎሰም አይሰማ" በሚል ርዕስ ያወጡትን የተምታታ ጽሑፍ ካነበቡት አንዱ ነኝ። ጽሑፉ የያዘው ቁምነገር ቢኖር የአማርኛው ጥራት ብቻ ነው።

ስለአመጽ አነሳስም ብዙ ካሉ በሁዋላ፣ አሁን በኢትዮጵያ አመጽ ለማካሄድ አይመችም በማለት የህብረተሰብ ሳይንስን ሊገቱ ይሞክራሉ። ለመክኔዮም በአንድነት የተደራጀ ህዝብ የለም በማለት ግፉንና ስቃዮን በይደር ለማቆየት ይሞክራል። የጋራ ችግር ያለበትንም ህዝብ፣ ወያኔ የከፋፈለው አንሶ በከረረ ቋንቋ ሊለያዩት ይሞክራሉ። ወደህዝባዊ አንድነት መምጣት የሚችሉትንም ኢትዮጵያዊን ታጋዮች ነጥለው በመጥራት ተራ ዘለፋ ያሰማሉ። ለአመጽ መነሳት በቂ ምክንያት እንዳለ እየመሰከሩ፣ ሌላ ምልክት ለማየት ይፈልጋሉ። አመለካከታቸው ድብልቅልቅ ያለ ነው። ወያኔስ ከዚህ የባሰ ምን ሊል ይችላል።

"የሰካራም ስድቡ ሰካራም ነው።" እንደሚባለውም በውጭ ያሉ የሕዝብ ወገኖችን ባልተሞረደ ብዕር ይዘልፋሉ። እጠቅሳለሁ፡ *"በተለይ ከኢትዮጵያ ውጭ ሆነው አመፁ መነሳሳት አለበት በማለት የሚቀሰቅሱ ግለሰቦችም ሆኑ ቡድኖች በየድረ-ገጹና በየሬዲዮ ጣቢያው እየቀረቡ ሲያቅራሩ (መስመር የእኔ) አድምጠናል። ከግብጽ ቀጥሎ የኢትዮጵያ ተራ ነው፤ ህዝቡን ለአመጽ ማነሳሳት ያስፈልጋል እያሉ የሚሞነጫጭሩ የወረቀት ነብሮችንም ታዝበናል። ይህ ግርግር አልኩ ከማለት አያልፍም። ሀገር ውስጥ ካለው ዜጋ በቀር የውጭ አዳማቂና አራጋቢ ከመሆን ያለፈ ምንም አስተዋፅዖ አይኖረውም። …"*

በማለት በውጭ ያለውን ታጋይ ከወገኑ ብሶት ባይተዋር ለማድረግ ይሞክራሉ። ሊያደርግ የሚችለውንም አስተዋጽዖ ሊያጣጥሉ ይጥራሉ። እየተስተዋለ እንጅ! ምን ዓይነት አይምሮ (አእምሮ) ነው?

ቀጥለውም "*በሀገራችን ያለው የጠባብ ብሄርተኛው አምባገነን መንግሥት የሚያደርሰው ሰቆቃና ጭቆና ህዝብ ሊሸከመው ከሚችለው በላይ እንደደረሰና አሁንም በቱኒዝያና በግብፅ ገንፍሎ እንደተነሳው የሕዝብ አመጽ በኢትዮጵያም ውስጥ በቅርቡ ሊነሳ እንደሚችል ምንም አጠያያቂ አይሆንም። … አሁንም በሀገራችን አመጽን አቀጣጣይ ሊሆን የሚችለውን ቀስቃሽ ምክንያት ዛሬ መተንበይ ባይቻልም እያሌ የሆኑ ክብሪቶች እሳቱን ለመጫር ቀናቸውን እየጠበቁ እንደሆኑ የኢትዮጵያን ሁኔታ በቅርብ ሆኖ ለተመለከተ የተሰወረ አይሆንም። የሚሆን ይሆናል። ማናቸውም ነገር ከመሆን አያግደውም።*" በማለት ስለማይቀረው አመጽ እራሳቸው ይናገራሉ። ታዲያ ሌሎቹም አቶ አይምሮ የሚዘልፏቸው ፀሐፊዎች ከዚህ የተለየ ምን ፃፉ? ምን ተናገሩ?

*ለመሆኑ "የሚፈርስ ከተማ ነጋሪት ቢጎሰም አይሰማ" የሚለውን ርዕስ ሲመርጡ ምን ማለት እንደሆነ ተረድተውታል? ቀስቃሽ አያስፈልግም ማለት ምን ማለት ነው? ደራሲ ከበደ ሚካኤል፡*

*በውቀት፣ በሥልጣኔ ግሎ ለመነሳት፣*
*ቆስቋሽ ይፈልጋል፣ የሰው ልጅ እንደ እሳት።*

*ያሉትን ይረዱት ይሆን?*

በአጠቃላይ የፅሑፋቸው ይዘት የራሳቸውን አመለካከት በራሳቸው ምስክርነት የሚያጋልጥ

ስለሆነ ሌሎችን ከመዝለፋቸው በበፊት ማንነታቸውን ይመርምሩ። አውቀውም ሆነ ሳይገነዘቡት ገደል የገቡ ይመስላሉ። ወይም ተቃዋሚዎችን በመወረፍ፣ እጅ መንሻ አቅርበው በማጣጣር ላይ ካለ አገዛዝ መጠጋት ፈልገው ይሆናል። "ወያኔና ውሃ ሲወስድ እያሳሳቀ ነው።"

ማንም ወደደ ጠላ የወያኔ አገዛዝ፣ አብሮነቱን ባከበረ ሕዝብ ትግል ይወገዳል። ይህም የቀጠሮ አማላጅ አያስፈልገውም።

አይምሮ ዳኛቸው ይሁናቸው!
ትግሉ ይቀጥላል!
ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!